**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)**

*Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

መጋቢት 4 ቀን 2004 ዓ.ም

# የመምህራን እንቅስቃሴ አድማሱ እየሰፋ ነው፡፡

የኢትዮጵያ መምህራን ባለፉት ሁለት ፈላጭ ቆራጭ መንግስታት የጭቆና ቀምበር ተጭኗቸው እንደነበር የሚታወስ ሲሆን ይደርስባቸው የነበረውን በደል በመቃወም በተለያዩ ጊዜያት አገር አንቀጥቅጥ አመጾችን ማካሄዳቸው በታሪክ የተመዘገበ ነው፡፡ ለንጉሣዊው ፈላጭ ቆራጭ ሥርዐት መናጥና መንኮታኮት ከኢትዮጵያ ላብ አደሮች፣ አርሶ አደሮች፣ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ባልተናነሰ መልኩ የኢትዮጵያ መምህራን ታግለዋል፡፡ ደማቸውን አፍሰዋል፡፡ ለመምህራን የሥራ ህይወት መሻሻል ፣ ለትምህርት ጥራትና ፍትሀዊ ሥርጭት፤ …ወዘተ ባካሄዱት እልህ አስጨራሽ ትግል ብዙዎች ተሰውተዋል፡፡ የኢትዮጵያ መምህራን  በ1966 ዓ.ም የአገሪቱን ብዙሃን ወጣት የከፍተኛ ትምህርት ዕድል የሚነፍገውንና  የመማር ፍላጎትን የሚገድበውን ሴክተር ሪቪው የተሰኘውን እቅድ በመቃወም ከዳር እስከ ዳር  በአንድ ላይ  የሥራ ማቆም አድማ መተው  ሕዝባዊ ትግሉን በማቀጣጠል "የስዩመ መለኮት" ዘመን ተንኮታኩቶ እንዲቀበር ጉልህ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ በ1966 ዓ.ም መምህራን የጀመሩት እንቅሰቃሴ በኢትዮጵያ ተማሪዎች በመታጀቡ ከቶውንም ሊበገርና ሊቀለበስ አልቻለም ነበር፡፡ በወቅቱ በተማሪዎችና በመምህራን ይዘመር የነበረው :

**"መሬት፣ መሬት፣ መሬት ለአራሹ ሊሰጠው ይገባል፤**
**በላቡ ያስተማረው ይሚገትለታል።**
**ደሀ፣ ደሀ ምን ታየበት፣**
**እንዳይማር የሆነበት።**
**ነፃነት፣ ነፃነት የምትሹ፣**
**ተዋጉለት አትሽሹ።"**

በዚህ ህዝባዊ እንቅስቃሴ በርካታ መምህራንና ተማሪዎች በጅማ፣ በደብረ ማርቆስ፣ በጎንደር፣ በመቀሌ፣ በደሴ፣ በአስመራ፣ በሸዋ ሮቢት፣ በዝዋይ፣ በወተር፣ በዓለማያ ፣ በጎባ፣ በጎሬ፣ በጊምቢ፣ በነቀምት፣ በአዲስ አበባ ታስረው ተቀጥቅጠዋል፤ አካለ ስንኩል ሆነዋል። ስቃዩ ሲበዛና ሲበረታ ትግሉ ይበልጥ እየጋለና እየጋመ ሄደ እንጂ ለአፍታም እንኳ አልረገበም ነበር፡፡ በመሆኑም ንጉሣዊውን ሥርዓት አራደ፣ አርበተበተ፣ ለመገርሰሡም የበኩሉን የትግል ክንድ አስተዋጽኦ አደረገ፡፡ ክብር ሞገስ በዚያ ዘመን ለነበሩና በትግሉ ለተሳተፉ መምህራንና ተማሪዎች !

በንጉሣዊው ፈላጭ ቆራጭ እግር የተተካው ወታደራዊ ፈላጭ ቆራጭ ሥርዓትም በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በአጠቃላይ በመምህራን ላይ በተለይ በርካታ ሰቆቃዊ ድርጊትን ፈጸመ፡፡ መምህራንን አሰረ፣ ገረፈ፣ በእሳት ጠበሰ፣ ሥጋቸውን በሳንጃ ወጋ፣ ባታቸውንና ክንዳቸውን በምሳር ጎማመደ፣ አንገታቸውን በሳንጃ አረደ፣ አናታቸውን በጥይትና በቆመጥ ነደለ፡፡ መምህራኑ ለነፃነት፣ ለዴሞክራሲ፣ ለአገራቸው ለኢትዮጵያ ክብር ይህን ሲሰሙት የሚዘገንን መከራን ተቀበሉ፡፡ የመከራውና የስቃዩ መበራከት የመምህራንን ትግል ሊገታው አልቻለም፡፡ ትግሉ በይፋ መሆኑ ቀርቶ በህቡዕ እንዲቀጥል የግድ ሆነና ፋሽስታዊው ወታደራዊውን መንግሥት ለመገርሰስ የድርሻውን አበርክቷል፡፡

ፋሽስታዊው የምርጥ መኮንኖች ወንበር ላይ የተኮፈሰው ሌላው ፈላጭ ቀራጭ ዘረኛ የሆነው የወያኔ ቡድንም በተራው የጭቆና ለበቁን በመምህራን ላይ አሳረፈ። የመጀመሪያ እርምጃው ነጻ የመምህራን ማህበር እንዳይኖርና የመምህራኑ ማህበር በቀጥታ የወያኔ አገልጋይ እንዲሆን ማድረግ ሲሆን ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ መምህራንን አስፈራራ፣ ከሥራ ፈነቀለ፣ አሰረ፣ ገደለ። የኢትዮጲያ መምህራንን ትግል ግን ማኮላሸት ከቶውንም አልቻለም። መምህራን ወያኔ የዘረጋውን የዘር፣ የሃይማኖት፣ እንዲሁም ሌሎችም የመከፋፈያ ቀያይ መስመሮችን አልፈው የጋራ ጉዳያቸው በሆነው በትምህርት ጥራት፣ በዴሞክራሲና በሰብዓዊ መብቶች በአንድ ላይ መነሳታቸውን በመስጋት ወያኔ በግዳጅ የአባልነት ፎርም እንዲሞሉ አደረገ። የመምህራን ሕይወትና ህልውና ከአጠቃላይ ከጉስቁሉ ኢትዮጵያዊ ወገናቸው የተለየ ባለመሆኑ በተናጠል የወያኔን ሥርዓት በተለያየ አጋጣሚ እየተጋተሩ ነው። በርካታ መምህራን የይስሙላ አባልነታቸውን በይፋ መልቀቃቸውን በማሳወቅ ከወያኔ መጠቀሚያነት ነፃ ሆነዋል። ይህ ሁኔታ ያሰጋው ወያኔ በያካባቢው ቅዳሜና እሁድ የወያኔ አባል የሆኑ መምህራንን በመሰብሰብ በየትምህርት ቤቱ አድማ ሊጠነስሱና ሊመሩ ይችላሉ ብለው የሚጠረጥሯቸውን መምህራን ስም እንዲያሳውቁ ትዕዛዝ ቢተላለፍም በአባሎቻቸውም እንኳ ትእዛዙ ሊከበር አልቻለም። የመምህራን ብሶት ከጣርያ በላይ በማለፉ በተለያዩ አካባቢዎች መምህራን በግልም በቡድንም መብታቸውን ለማስከበር እያመጹ ነው። ይህን የመምህራን መነሳሳት ለማኮላሸትና ለመግታት ወያኔ መምህራንን ከሥራ እያባረረ ፣ የተወሰኑትንም እያሰረ ባለበት በዚህ ወቅት የመምህራን የመብት ጥያቄ እንቅስቃሴ እየጋመና እየሰፋ በመሄድ ላይ ይገኛል።

የኔ ሰው ገብሬ እራሱን አቃጥሎ የተሰዋው በሌላ ሳይሆን በወያኔ የግፍ አገዛዝ ተማሮ ነው። በቅርቡ በጎንደር ደምቢያና ቆላድባ የተጀመረው የመምህራን አመጽ በሌሎች አካባቢዎችም እየተዛመተ ነው። ለነፃነት የሚደረግ አመጽ እንደ ሰደድ እሳት እየሰፋና እየጎለበተ መሄዱ አይቀሬ ነው። ሰሞኑን ታች አርማጨሆና ደባርቅ በሚገኙ ት/ቤቶች መምህራን መብታቸውን ለማስከበር በአንድነት መንቀሳቀሳቸውንና በዚህም ሳቢያ በአካባቢው የሚገኙ ት/ቤቶች እንደተዘጉ ተረድተናል። አመጹን አነሳስተዋል በሚል መምህር ገብሬ፣ መምህር ወርቃየ፣ መምህር ተገኝ፣ መምህር ወርቁ መታሰራቸውን ከደረሰን መረጃ ተገንዝበናል። በአካባቢው ያሉ መምህራን የታሰሩት ካልተፈቱ ሥራ እንደሚያቆሙ አሳውቀዋል። ይህ የመምህራን አመጽ እየዋለ አያደረ እንደ ቋያ እሳት በመላው አገር እንደሚሰፋ የታመነ ነው።

ኢህአፓ ከትላንት እስከ ዛሬ የትግል ዝናሩን ሳያላላ ለጉስቁሉና ለተገፋው ህዝብ ታግሏል ወደፊትም ይታገላል። በየትኛውም አካባቢ መብታቸውን ለማስከበር ከሚታገሉ መምህራን ጎን ይቆማል።

የመምህራን አመፅ ይፋፋም!

የመምህራን መብት በተባበረ ትግላቸው ይከበራል!


EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France